# <u>የሚለንየም ቦንድ እና የኢትዮጵያ እድገት</u>

**ከ ዮሐንስ**

ለዚህች አጭር ጽሁፌ መነሻ ያደረግኩት«ፕሮፌሰር ሰይድ ሃሰን» የተባሉ ግለሰብ *«የኢትዮጵያ ኃይል ኮርፖሬሽን ለዲያስፖራው ሕብረሰተብ ለመሸጥ ስላወጣው ማስታወቂያ አንዳንድ አመላካች ሃሳቦች»* በሚል ያሰፈሩት ጽሑፍን ነው፡፡

ስለ ሚለንየም ቦንድ ምንነትና ዓላማ በባለቤትነት በያዘው የኢትዮጵያ መብራትና ኃይል ኮርፖሬሽን የተሰጠው ማብራርያ ከገላጭም በላይ ስለሆነ ስለቦንዱ ማብራርያ መስጠት አልፈልግም፡፡ ይልቁንም «ጸሐፊው» ስላነስዋቸው አንዳንድ ሃሳቦች ላይ የራሴን አስተያየት ላስቀምጥ፡፡

«ጸሐፊው» የሚለንየም ቦንድን በተመለከተ በባለቤቱ ከተነገረን ውጪ በውጭ አገር ስለሚኖሩ ብቻ ከሌሎች ተለይቶ በተሰጣቸው ጸጋ የተገለጠላቸውን ራዕይ ዘርዝረው ለማስረዳት ሲሞክሩ ቦንዱን ለመግዛት መላኪያ ይከፈላል፤ ወይም ቦንዱን ለመግዛት ወደ አገር ቤት ሲኬድ ወጪ ስለሚያስወጣ ይቅርባችሁ ብለው በራዕይ የተገለጠላቸውን የዘመኑ ታላቅ የምጣኔ ሃብት ትንተናቸውን አቅርበዋል፡፡

«ጸሐፊው» የመጻፍና ሃሳባቸውን የመግለጽ መብት ስላላቸው መጻፋቸውን አልቃወምም ፡፡ የምቃወመው እውነታን በመሸፈን የዳያስፖራው ተቆርቋሪ መስለው የቀረቡበት ስልታቸውን ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት አገራችን ሰጥማበት ከነበረው የድህነት መቀ-መቅ ቀስ በቀስ አላቅቆ አሁን ወደምናየው የልማትና የእድገት ደረጃ አድርሷታል ፡፡ የካሁን በፊቱ በማየትም ለወደፊቱ ከዚህ የበለጠ እንደምናይ አልጠራጠርም ፡፡ መንግስት በ11 % እድገት ይኖራል ብሎ ሲያበቃ በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት አይ ኤም ኤፍ 6.5 % ነው ብሏልና በኢትዮጵያ እድገት የለም ብለው ከሚያምኑት ወገን በመሆናቸው እንዲህ በማለቴ «ጸሐፊው» ላይስማሙ ይችላሉ ፡፡

አገራችን አሁን በተያያዘችው የእድገት ጎዳና ስትራመድ በውስጥም በውጭም ያለ ኢትዮጵያዊ፤ ትውልደ ኢትዮጵያዊ እና የኢትዮጵያ ወዳጅ ያቅሙን ሁሉ እንዳበረከተ ገሃድ ነው፡፡ ለወደፊቱም አገሩን ለማሳደግ እንደሚረባረብ እምነቴ ነው ፡፡ በዚህም የተነሳ እያንዳንዱ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ(በነገራችን ላይ ኢትዮጵያዊ ስል አንድን የኢትዮጵያ ከተማ ከአንድ የውጭ አገር ከተማ ለማነጻጸር የሚቀርቡ ሃሳቦችን ተቃውመው ሰልፍ የሚወጡትንና ለእንደዚህ አይነት ዘረኛ ተግባር የተሰለፉትን አይጨምርም ፡፡ ምክንያቱም  ኢትዮጵያን የሚቃወም ኢትዮጵያዊ ሊሆን አይችልምና፡፡) ኢትዮጵያችንን የሚያሳድግ እስከሆነ ድረስ በቦንድም ሆነ በሌላ መንገድ«ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልምና» የቻለውን ያደርጋል ፡፡

እዚህ ላይ አንድ መነሳት ያለበት ጉዳይ አለ ፡፡ ኢትዮጵያችን አሁን የምናወራለትን የሚለንየም ቦንድ ስለቀረ ከእድገትዋ ትስተጓጎላለች ብለው የሚያስቡ የዋሃን ካሉ ሳይመሽባቸው እንዲያስቡበት የወንድም ሃሳቤን እንካችሁ እላለሁ ፡፡ ይልቁንም ሁሌም አፍሽ የሆነውን የጭፍን ተቃውሞና የዘረኝነት አባዜ አባትና አናዛዥ ሆኖ ከማለፍ አገራችን የምትጠብቀውን እና ለማየት የምትመኘውን ልማትና እድገት ለማፋጠን ጠንካራ ወገን መሆን አስተዋይነት ይመስለኛል ፡፡ ካልሆነ ኢትዮጵያችን አሁንም ከማደግ ወደኃላ አትልም ፡፡ እስካሁን የተገኘው እድገት በሚለንየም ቦንድ በተገኘ ዶላር ነበረ እንዴ?

በመቀጠል «ጸሐፊው» ስለ ግሽበት ያሰሉትን ስሌት ለአዋቂዎች ልተወውና መንግስት ዋስትና የሰጠበትን ቦንድ መግዛት ማለት ገንዘባቹህን ሜዳ ላይ እንደጣላችሁ ቁጠሩት አሉ ። ሚስጢር አወጣህ አትበሉኝ እንጂ እንደዚህ አይነት መሰረተ ቢስ ወሬ የሚያወሩ ሰዎች በየተሰማሩበት ለቁምነገር ያልታደሉትን እንደሆኑ አውቃለሁ ። በቁም ነገር ፈንታ አሸሼ ገዳሜ ሲል ገንዘቡንና ጊዜውን ያባከነ ብኩን ወደ አገር ቤት ገብቶ ኢንቨስት ለማድረግ የሚያስብ ሰው ሲያጋጥመው የመጀመርያው ቤተሰባዊ ምክሩ «ወያኔ ይበላሃል» ነው ። ወደ ትውልድ አገሩ ገብቶ እድገት የሚያመጣ ተግባር ከሚያከናውን ገንዘብህን የዎል ስትሪት ሞንስተር አመድ ያድርገው ይለዋል ። በዚህም አያበቃም እንደምንም የሚያጋጥሙዋቸውን መሰናክሎች አልፈው አገር ቤት ገብተው የተሳካ ስራ ሲሰሩ «የወያኔ ደጋፊ ስለሆነ…» የሚል ቅጽል ስም ይቀጸልላቸዋል ። «ተረታን እንዳይሉ ይግባኝ ይላሉ» እንደሚባለው «ጸሐፊው»  ቁም ነገር የሚሰሩበትን ጊዜያቸውን እና ገንዘባቸውን እንደዚህ አይነት ስም የሌለው ጽሑፍ በመጻፍ ስለሚያጠፉትና እሳቸው ኢንቨስት ማድረግ ካልቻሉ ደግሞ ሌላውም እንደሳቸው ብኩን መሆን ስላለበት የ«ባልበላውም ጭሬ አፈሰዋለሁ» ፕሮፓጋንዳቸውን ይቀጥላሉ።

ሌላው ማንሳት የምፈልገው ነጥብ «ጸሐፊው» የግልገል ጊቤው ቅሌት ያሉትን ነው ። ምናልባት በሚኖሩበት አከባቢ«የዋተር ጌት ቅሌት፤ የማድኦፍ ቅሌት ወዘተ ሲባል ስለሰሙ እሳቸውም  ቅሌት የሚለውን ቃል ለመጥቀስ ፈልገው ከሆነ መልካም ። ካልሆነ ግን እንዴት ነው ነገሩ የቅሌት ትርጉም ተለወጠ እንዴ? ያስብላል ። ለነገሩ ለነ«ምንተስኖት» ምን ይሳናቸዋል? አገርን ከድህነትና ኃላ ቀርነት የሚያላቅቅ ፕሮጀክት መስራትና መተግበር ከቅሌት ተቆጠረ? አገራቹህን ለመገንባት አንድ ድንጋይ ሳታነሱ እድሜያቹህን በወሬ የጨረሳችሁ ምን ስም ሊሰጣችሁ ይሆን?

የሚገርመው ነገር «ጸሐፊው» ያነሱት ጉዳይ ሰሞኑን የቢቢሲ የዜና ማሰራጫ ሲያወራው ሰንብቷል ። ይሄው የዜና ማሰራጫ ከጥቂት ወራት በፊት አሁን ግድብ በሚሰራበት ክልል ሕጻናት ተራቡ ብሎ የመቼ አመተ ምሕረት ፊልም እንደሆነ አላውቅም የከሳ ሕጻን ምስል ሲያሳይ ነበር ። ታድያ በዚያን ጊዜ ለምግብ እጥረቱ ምክንያቱ መንግስት ዘላቂና አስተማማኝ ፖሊሲና ፕሮጀክቶች ስለሌሉት ነው ብሎ ሲያትት ነበር ።

መንግስት የአገሪቱን የኃይል ፍላጎት በአስተማማኝ ሁኔታ በማሟላት በተጓዳኝ ሰፋፊ ሜካናይዝድ የእርሻ ማሳዎች ሊያለማ የሚችል ፕሮጀክት ቀርጾ ወደ ትግበራ ሲገባ ይህ የዜና ማሰራጫ «ሕዝብ የከፋፈለ…» ብሎ ሰየመው ። የውጭዎቹ እንደዚህ አይነት ወሬ የሚያወሩት ያደረ ቂም ኖሯቸው ወይም ለወደፊቱ ከሚያልሙት ጋር አልሄድ ብሏቸው ይሆናል ። የሚያሳዝነው ግን «የዋሁ ጸሐፊ» ለምንና ለማን መሳርያ እየሆኑ እንደሆኑ ሳይገባቸው ኢትዮጵያዊ ነኝ እያሉ ኢትዮጵያን የፊጢኝ አስሮ ወደ ኃላ የሚያስቀርን ትንተና ጠበቃና ተሟጋች ሆነው ቁጭ አሉ ። ትዝብት ብቻ።

ለማጠቃለል፤ አገራችን መበልጸግዋ አይቀርም ። ለመበልጸግ በምታደርገው ትግል አጋርና ተሳታፊ የሆኑት ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስረክብዋት ኢትዮጵያን እያዩ በዋጋ የማይተመን የህሊና እርካታ ያገኛሉ ። ጀግንነትስ ይሄው አይደል ?

በአንጻሩ ደግሞ ለኢትዮጵያ እርዳታ እንዳትሰጡ፤በኢትዮጵያ ኢንቨስት አታድርጉ፤ወደ አገር ቤት አትሂዱ፤የምትኖሩበትን አከባቢ ከአንድ የኢትዮጵያ ከተማ ለመጎዳኘት ሲሞክር የተቃውሞ ሰልፍ  ውጡ፤ የኢትዮጵያን መሪ ከሌሎቹ የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ አፍሪካን ወክሎ በስብሰባ እንዲሳተፍ ሲመረጥ «አበጀህ የኛ ልጅ፤እንዲህ ነው ኢትዮጵያዊ» እንደ ማለት ለምን ተመረጠ ብለው የሚቃወሙ፤ባጠቃላይ ኢትዮጵያን ሊጠቅም የሚችል ማናቸውም ተግባር ያከናወነ የተለየ ይሁን ብለው ሲሰብኩ የሚኖሩ ሰዎችም የተፈጥሮ ሕግ ነውና እነሱም ወልደው ለልጆቻቸው ኢትዮጵያን ለማስረከብ መሰለፋቸው አይቀርም ። ግን ያኔ ምን ይላሉ ?